የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

፴፪ኛ ዓመት ቁጥር ፵፪
አዲስ አበባ ሐምሌ ፲፮ ቀን ፪ሺ፲፰

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

32nd Year No. 42
ADDIS ABABA, 23rd July, 2026

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፬፻፳፭/፪ሺ፲፰

የጉምሩክ አዋጅ (እንደተሻሻለ) እንደገና ለማሻሻል የወጣ አዋጅ.....................................ገጽ ፲፱ሺ፰፻፶፮

Content

Proclamation No. 1425/2026

Customs Proclamation (as Amended) Further Amendment………………………Page 19856

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፬፻፳፭/፪ሺ፲፰

የጉምሩክ አዋጅን እንደገና ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

የገቢ እና የወጪ ንግድ ይበልጥ የተቀላጠፈ እንዲሆን ማድረግ፣ የጉምሩክ ስርዓት ኢትዮጵያ ከፈረመቻቸው አለም ዓቀፍ ስምምነቶች እንዲሁም አህጉራዊ እና ቀጣናዊ ስምምነቶች ጋር የተጣጣመ እንዲሆን ለማድረግ፣ አስመጪዎች በቀረጥ እና ታክስ አወሳሰን ረገድ ያላቸውን አቤቱታ በማቅረብ ረገድ የነበረባቸውን መሰናክል ለማስወገድ የጉምሩክ አዋጅን ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የኮንትሮባንድ ንግድ ስራን ለመከላከል የሚያስችሉ ተጨማሪ ድንጋጌዎችን በአዋጁ ዉስጥ ማካተት የኮንትሮባንድ ንግድን ለመከላከል የሚያስችል በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግስት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት የሚከተለው ታውጇል።

PROCLAMATION No.1425/2026

CUSTOMS PROCLAMATION (FURTHER AMENDMENT) PROCLAMATION

WHEREAS, it has become necessary to amend the Customs Proclamation to facilitate import and export trade, align the customs system with the international, continental and regional agreements to which Ethiopia is a party, remove obstacles faced by importers in challenging customs duty and tax determinations ;

WHEREAS, it is believed that adding additional legal provisions in the Proclamation will help combat contraband trade;

NOW THEREFORE, in accordance with Article 55 Sub-Article (1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia it is hereby proclaimed as follows.

ያንዱ ዋጋ
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

፩. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ "የጉምሩክ አዋጅ (እንደተሻሻለ) እንደገና ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፬፻፳፭/፪ሺ፲፰" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪. <u>ማሻሻያ</u>

የጉምሩክ አዋጅ ቁጥር ፰፻፶፱/፪ሺ፮ (እንደተሻሻለ) እንደሚከተለው እንደገና ተሻሽሏል፡-

፩) የአዋጁ አንቀጽ ፳፫ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፩)፣ (፪)፣ (፫) እና (፬) ተተክቷል ሌሎች የአንቀጹ ድንጋጌዎች ከንዑስ አንቀጽ (፭) እስከ (፲፩) በመሆን ተሸጋሽገዋል፡-

፩/ ኮሚሽኑ የሚለቀቁ ዕቃዎች በተመዘገበ ዲክላራሲዮን የተሸፈኑ መሆናቸውን ለማረጋገጥ እና ቀጣይ የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓትን ለመፈፀም የእቃዎቹን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ወይም በመመሪያ በሚወሰን መጠን ናሙናዎችን በመውሰድ መመርመር ይችላል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የሚከናወን የዕቃ ምርመራ እንደ አስፈላጊነቱ በዕቃ መፈተሻ መሳሪያ ወይም በላቦራቶሪ ወይም በአካላዊ ወይም በሌላ አማራጭ ሊከናወን ይችላል፡፡

፫/ ኮሚሽኑ በዲክላራሲዮን አቅራቢው የቀረበ የዕቃ ዲክላራሲዮን ላይ የሰፈሩ መረጃዎችን ትክክለኛነት እና የተሟሉ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የሰነድ ምርመራ ሊያከናውን ይችላል፡፡

1. <u>Short Title</u>

This proclamation may be cited as "Customs Proclamation (as Amended) Further Amendment No. 1425/2026".

2. <u>Amendment</u>

The Customs Proclamation No.859/2014 (as amended) is hereby further amended as follows:

1) Article 23 Sub-Article (1) of the Proclamation is deleted and replaced by the following new Sub-Articles (1), (2), (3), and (4); other provisions of the Article are renumbered as Sub-Articles 5 to 11:

1/ The Commission may, in order to ensure that goods to be released are covered by a registered declaration and to carry out subsequent customs procedures, examine the goods in whole or in part or by taking samples in quantities to be determined by a Directive.

2/ Examination of goods conducted in accordance with Sub-Article (1) of this Article may, as necessary, be carried out by cargo scanning equipment or laboratory analysis or physical inspection or other alternatives.

3/ The Commission may conduct a documentary examination to verify the accuracy and completeness of the information contained in the goods declaration submitted by the declarant.

፬/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ኮሚሽኑ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው አስቀድሞ የዕቃ እና/ወይም የሰነድ ምርመራ በተከናወነባቸው ዕቃዎች ላይ በድጋሚ ምርመራ ሊያከናውን ይችላል፡፡

፪) የአዋጁ አንቀጽ ፳፭ ንዑስ አንቀጽ (፬) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፬) ተተክቷል፤ እንዲሁም ከንዑስ አንቀጽ (፬) ቀጥሎ አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፭) ተጨምሯል፤

፬/ በአንድ ዲክላራሲዮን ተመዝግበው ወደ አገር የገቡ ዕቃዎች ለነጻ ዝውውር መለቀቅ ያለባቸው በአንድ ላይ ነው፡፡

፭/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) ድንጋጌ ቢኖርም ዲክላራሲዮን አቅራቢው ወደ አገር ለገቡ ዕቃዎች ሊከፈል የሚገባውን ቀረጥና ታክስ በአንድ ጊዜ መክፈል እንደማይችል ገልፆ ዕቃዎች በክፍልፋይ እንዲለቀቁ ጥያቄ ያቀረበ እንደሆነ ኮሚሽኑ በክፍልፋይ ለሚለቀቀው ዕቃ መጠን ሊከፈል የሚገባው ቀረጥና ታክስ መከፈሉ ሲረጋገጥ ዕቃዎች በክፍልፋይ እንዲሊለቀቁ ሊፈቅድ ይችላል፡፡

፫) የአዋጁ አንቀጽ ፶፩ ንዑስ አንቀጽ (፩)፣ (፪)፣ (፯) እና (፰) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፩)፣ (፪)፣ (፯) እና (፰) ተተክቷል፤

፩/ መዘግየቱ የተፈጠረው በጉምሩክ ቁጥጥር፤ በአስተዳደራዊ እርምጃ ወይም ከአቅም በላይ በሆነ ሁኔታ በመሆኑ ምክንያት ጊዜው ካልተራዘመ በስተቀር ማናቸውም በባህር ወይም በየብስ ተጓጉዞ ወደ አገር የገባ ዕቃ ጊዜያዊ የጉምሩክ ዕቃ ማከማቻ ከገባበት ቀን ጀምሮ በአርባ አምስት ቀናት ውስጥ አስፈላጊው የጉምሩክ ሥነሥርዓት ተከናውኖበት ከማከማቻው መውጣት አለበት፡፡

4/ Without prejudice to the provisions of Sub-Article (2) of this Article, the Commission may, where it finds it necessary, conduct a re-examination of goods that have already undergone goods and/or documentary examination.

2) Sub-Article (4) of Article 25 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new Sub-Article (4); additionally, Sub-Article (5) is added after Sub-Article (4) ;

4/ Goods entered into the country and registered under a single declaration shall be released for free circulation together.

5/ Notwithstanding the provisions of Sub-Article (4) of this Article, where the declarant states that he is unable to pay the duties and taxes due on the imported goods at once and requests a partial release of goods, the release of goods upon verification that the duties and taxes due for the specific portion of goods to be released have been paid.

3) Sub-Articles (1), (2), (7), and (8) of Article 51 of the Proclamation are deleted and replaced by the following new Sub-Articles (1), (2), (7), and (8) ;

1/ Any goods imported by sea or land must be removed from the temporary customs storage within forty-five days from the date of entry into the storage after the necessary customs formalities have been completed, unless the delay is attributable to customs controls, administrative action, or force majeure, in which case the time limit shall be extended accordingly.

፪/ በዚህ ንዑስ አንቀጽ (፩) በተገለጹት ተመሳሳይ ልዩ ሁኔታዎች ምክንያት ጊዜው ካልተረራዘመ በስተቀር ማናቸውም በአየር ተጓጉዞ ወደ አገር የገባ ዕቃ ወደ ጊዜያዊ የጉምሩክ ዕቃ ማከማቻ ከገባበት ቀን ጀምሮ በሰላሳ ቀናት ውስጥ አስፈላጊውን የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ተከናውኖበት ከማከማቻው መውጣት አለበት፡፡

፯/ ወደ ጊዜያዊ የጉምሩክ ዕቃ ማከማቻ ወይም ቦንድድ መጋዘን የገባ ዕቃ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩)፣ (፪) ፣ (፫) እና (፬) በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ካልወጣ ወደ መንግሥት የጉምሩክ መጋዘን እንዲዛወር ይደረጋል፡፡

፰/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፯) መሰረት ወደ መንግስት የጉምሩክ መጋዘን የገቡ ዕቃዎች ከመወገዳቸው በፊት የዕቃው ባለቤት ሊከፈል የሚገባውን ቀረጥና ታክስ እንዲሁም ሌሎች ወጪዎችን በመክፈል ዕቃዎችን የመረከብ መብት ይኖረዋል፡፡

፬) የአዋጁ አንቀጽ ፷፪ ንዑስ አንቀጽ (፪) ፊደል ተራ /ሀ/ እና /ለ/ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፪) ፊደል ተራ /ሀ/ እና /ለ/ ተተክቷል፤

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ፊደል ተራ (ሀ) ድንጋጌ ቢኖርም ኮሚሽኑ፡-

(ሀ) አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ቅርስ ሊባሉ የሚችሉ ዕቃዎችን ወይም የገንዘብ ሚኒስቴር በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ጥቅም ላይ ሊውሉ ይገባል የሚላቸውን ዕቃዎች አግባብ ላለው የመንግስት ተቋም ያስተላልፋል፤

2/ Any goods imported by air must be removed from the temporary customs storage within thirty days from the date of entry into the storage, after the necessary customs formalities have been completed, subject to the same exceptions provided under Sub-Article (1) of this Article.

7/ Goods entered into temporary customs storage or a bonded warehouse that are not removed within the time limits specified under Sub-Articles (1), (2), (3), and (4) of this Article shall be transferred to a government customs warehouse.

8/ The owner of the goods shall have the right to take delivery of the goods transferred to a government customs warehouse in accordance with Sub-Article (7) of this Article before they are disposed of, upon payment of the duties, taxes, and other expenses due.

4) Sub-Article (2) paragraph (a) and (b) of Article 62 is deleted and replaced by the following new Sub-Article (2) paragraph (a) and (b) ;

2/ Notwithstanding the provisions of Sub-Article (1) paragraph (a) of this Article, the Commission:

(a) Goods qualifying as cultural heritage under the relevant law, or goods designated by the Ministry of Finance for use by government institutions, shall be transferred to the appropriate public institution;

(ለ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በኮንትሮባንድ ከሚያዙ እቃዎች ሽያጭ የሚገኘው ገቢ የገንዘብ ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ለአቅም ግንባታ ተግባር ይውላል።

፭) የአዋጁ አንቀጽ ፹፱ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፹፱ ተተክቷል፣

፹፱. መርሆዎች

፩/ በሕግ መሰረት ወደ አገር በሚገቡ እና ወደውጭ አገር በሚላኩ እቃዎች ላይ ለሚከፈለው የጉምሩክ ቀረጥ፣ ሌሎች በገቢ እና ወጪ እቃዎች ላይ የሚጣሉ ክፍያዎች እና ታሪፍ ነክ ላልሆኑ እርምጃዎች መሰረት የሚሆነው የጉምሩክ ዋጋ ስሌት የሚወሰነው በዚህ የአዋጁ ክፍል በተመለከቱት የዋጋ ስሌት ዘዴዎች መሰረት ይሆናል።

፪/ ወደ አገር የሚገባ ማናቸውም ዕቃ የጉምሩክ ዋጋ የሚወሰነው እንደ ቅደም ተከተላቸው በዚህ አዋጅ ከአንቀጽ ፺ እስከ ፺፭ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሰረት ነው፡፡

፫/ ወደ ውጭ አገር ለሚላክ ዕቃ የጉምሩክ ዋጋ ተደርጎ የሚወሰደው ዕቃው የተሸጠበትና ከኢትዮጵያ መውጫ እስከሆነው የጉምሩክ በር ድረስ ለማጓጓዝ የሚያስፈልገው ወጪ ድምር ይሆናል።

(b) Subject to Sub-Article (1) of this Article the proceeds from the sale of contraband goods shall be used for building capacity in accordance with the Directive to be issued by the Ministry of Finance.

5) Article 89 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new Article 89;

89. Principles

1/ The customs value of imported and exported goods, for the purposes of applying the customs tariff, other import or export charges, and non-tariff measures prescribed by law, shall be determined in accordance with the valuation methods set out in this Part.

2/ The customs value of imported goods shall be determined in accordance with Art. 90 -95 of this Proclamation, in the order of precedence.

3/ The customs value of export goods shall be the actual cost of the goods up to the final exit point from the customs territory of Ethiopia.

፮) የአዋጁ አንቀጽ ፹፱ ንዑስ አንቀጽ (፬) እና (፭) ተሰርዘው በሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፬) እና (፭) ተተክተዋል፤

፬/ ሚኒስቴሩ በዚህ አዋጅ የተደነገጉትን የዋጋ ዘዴዎች ስራ ላይ ለማዋል የሚያስችል መመሪያ ሊያወጣ ይችላል። ይህ መመሪያ በዚህ አዋጅ ከአንቀጽ ፺-፺፭ ከተመለከቱት ውጪ ሌሎች የዋጋ አተማመን ዘዴዎች ስራ ላይ እንዲውሉ ለመፍቀድ ወይም ለማዘዝ አይችልም።

፭/ ኮሚሽኑ ለስጋት ስራ አመራር እና ዋጋን ለማረጋገጥ የሚያገለግል የዋጋ መረጃ ቋት ሊያደራጅ ይችላል፤ ይህ የመረጃ ቋት እንደ ቁርጥ ዋጋ ወይም መነሻ ዋጋ ወይም በዚህ አዋጅ የተደነገጉትን የዋጋ ዘዴዎች የሚተካ ሆኖ ሊያገለግል አይችልም፤ ከዚህ የመረጃ ቋት የሚገኘው መረጃ በዲክላራሲዮን አቅራቢው የቀረበው የግብይት ዋጋ ምክንያታዊ መሆን አለመሆኑን ለመገምገም እና ተጨማሪ ማጣራት ማድረግ የሚያስፈልግ መሆኑን ለመወሰን ብቻ ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል።

፯) የአንቀጽ ፺ ንዑስ አንቀጽ (፩) መግቢያ እና የዚሁ አንቀጽ ፊደል ተራ (መ) ተሰርዘው በሚከተለው ተተክተዋል፤

፩/ ወደ አገር ውስጥ ለሚገባ ዕቃ የግብይት ዋጋ ተደርጎ የሚወሰደው ወደ ኢትዮጵያ እንዲላክ ለተሸጠው ዕቃ በትክክል የተከፈለው ወይም የሚከፈለው ዋጋ ሲሆን፤ አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፺፮ የተመለከቱት ተጨማሪ ክፍያዎች የታከለበት ይሆናል፤ ሆኖም:-

6) Sub-Article (4) and (5) of Article 89 are deleted and replaced by the following Sub-Article (4) and (5) ;

4/ The Ministry may issue a Directive for the implementation of the valuation methods provided under this Proclamation. Such Directive shall not establish or authorize any valuation method other than those set out in Articles 90 to 95.

5/ The Commission may use valuation databases for risk management and value verification; Such databases shall not serve as fixed or minimum values, nor replace the valuation methods established under this Proclamation; Information derived from these sources may be used solely to assess whether a declared transaction value appears reasonable and to determine whether further inquiry is warranted.

7) The introduction part of Article 90 Sub-Article (1) and pragraph (d) of the same Article are deleted and replaced by the following;

1/ The transaction value of imported goods shall be the price actually paid or payable for the goods when sold for export to Ethiopia, and adjusted where necessary, as set forth in Article 96 of this Proclamation; provided; however that:

(መ) ገዥዉና ሻጩ ግንኙነት ያላቸው ከሆነ እና ኮሚሽኑ በሁለቱ መካከል ያለው ግንኙነት በዋጋው ላይ ተጽዕኖ አሳድሯል ብሎ ለማመን በቂ ምክንያት ካለው በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፺፱ የተመለከተውን ሥርዓት በመከተል አስመጪው ባቀረበው የግብይት ዋጋ ላይ ጥያቄ ሊያቀርብ ይችላል፤ አስመጪው ግንኙነቱ በዋጋው ላይ ተጽዕኖ ያለማሳደሩን ማረጋገጥ ካልቻለ ኮሚሽኑ የቀረበውን የግብይት ዋጋ ውድቅ ሊያደርግ ይችላል።

፰) ከአንቀፅ ፺፰ ንዑስ አንቀጽ (፫) ቀጥሎ የሚከተሉት አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፬)፣ (፭) እና (፮) ተጨምረዋል፤

፬/ ሶፍትዌር የተጫነባቸው ወደ አገር የሚገቡ የመረጃ ማከማቻዎች የጉምሩክ ዋጋ የሚወሰነው በመረጃ ማከማቻ ዋጋ ወይም ወጪ ላይ ብቻ በመመስረት ይሆናል።

፭/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) ተግባራዊ ሲሆን፣ የመረጃ ሶፍትዌር ላይ ሶፍትዌር ዋጋ ወይም ወጪ ከጉምሩክ ዋጋ ላይ መቀነስ አለበት፤ ይህ የዋጋ ቅናሽ ተፈጻሚ የሚሆነው፣ አስመጪው የሶፍትዌሩን ዋጋ የመረጃ ሶፍትዌሩን ዋጋ በግልጽ ለይቶ የሚያሳይ መረጃ ሲያቀርብ ብቻ ነው፡፡

(d) Where the buyer and seller are related, the Commission may question the acceptability of the declared transaction value where it has reasonable grounds to believe that the relationship influenced the price, following the procedure set out in Article 99 of this Proclamation; If the importer is unable to prove that such relationship did not influence the price, the Commission may reject the declared transaction value.

8) The following new Sub-Articles (4), (5) and (6) are added after Sub-Article (3) of Article 98**;**

4/ The customs value of imported carrier media bearing software shall be determined based solely on the cost or value of the carrier medium itself.

5/ When Sub-Article (4) of this provision is applied, the cost or value of the software recorded on the carrier medium shall be deducted from the customs value; This deduction shall only be applicable if the declarant provides information that clearly distinguishes the cost or value of the software from the cost or value of the physical carrier medium.

፮/ ለዚህ አንቀጽ፡-

(ሀ) “**የመረጃ ማከማቻ**” ማለት ሶፍትዌርን ለማከማቸት እና ለማስተላለፍ ተብሎ የተሰራ እንደ ማግኔቲክ ዲስክ፣ ኦፕቲካል ዲስክ ወይም ቴፕ ያሉ የሚጨበጡ ቁሶች ማለት ነው፤ ይህ ትርጓሜ የተቀናጁ ሰርኪዩቶችን፣ ሴሚኮንዳክተሮችን እና መሰል መሣሪያዎችን እንዲሁም እነዚህ ሰርኪዩቶች ወይም መሣሪያዎች የተገጠሙባቸውን ማናቸውንም ሌሎች ቁሶች አያካትትም።

(ለ)“**መረጃ ወይም መተግበሪያ ሶፍትዌር**” ማለት ለመረጃ ማቀነባበሪያ መሣሪያዎች አገልግሎት እንዲውሉ ተብለው የተቀረጹ ፕሮግራሞች ወይም ትዕዛዞች ማለት ነው፤ ይህ ትርጓሜ የድምፅ ቅጂዎችን፣ ሲኒማቶግራፊክ ፊልሞችን እና የቪዲዮ ቅጂዎችን አያካትትም።

፱) የአዋጁ አንቀጽ ፺፱ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፺፱ ተተክቷል፤

፺፱. ተጨማሪ መረጃና ማስረጃ ስለማቅረብ

፩/ ኮሚሽኑ የቀረበው የግብይት ዋጋ የተከፈለውን ወይም ሊከፈል የሚገባውን ትክክለኛ ዋጋ የማያንጸባርቅ መሆኑን ወይም በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፺ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሰረት በገዢው እና በሻጩ ያለው ግንኙነት በግብይቱ ዋጋ ላይ ተጽእኖ ያሳደረ መሆኑን ለማመን በቂ ምክንያት ካለው ዲክላራሲዮን አቅራቢው የግብይቱ ዋጋ ትክክለኛ መሆኑን የሚያሳይ ተጨማሪ መረጃ ወይም ማስረጃ እንዲያቀርብ ሊጠይቀው ይችላል።

6/ **for the purpose of this Article:**

(a) “**Data carrier**” means a physical object, such as a magnetic disc, optical disc, or tape, designed for the storage and conveyance of software;This definition excludes integrated circuits, semiconductors and similar devices, as well as any articles into which such circuits or devices are incorporated.

(b) “**Data or instructions (Software)**” means recorded programs or instructions, supplied for the operation of data processing equipment; This definition excludes sound recordings, cinematic films, and video recordings.

9) Article 99 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new Article 99;

99. Production of Additional Information and Evidence

1/ Where the Commission has reasonable grounds to believe that the declared transaction value may not reflect the price actually paid or payable, or that the buyer-seller relationship may have influenced the price as per Sub-Article (2) of Article 90, it may require the declarant to produce additional information or evidence demonstrating that the declared transaction value is correct.

፪/ ኮሚሽኑ የዲክላራሲዮን አቅራቢውን ተጨማሪ መረጃ ወይም ማስረጃ ከተቀበለ በኋላም ስለግብይቱ ዋጋ በበቂ ምክንያት ላይ የተመሰረተ ጥርጣሬ ካለው ወይም ዲክላራሲዮን አቅራቢው ምላሽ ካልሰጠ የዕቃው የጉምሩክ ዋጋ በዚህ አዋጅ ከአንቀጽ ፺፩ እስከ ፺፭ ባሉት ድንጋጌዎች መሰረት ይወሰናል።

፫/ ዲክላራሲዮን አቅራቢው በሚያቀርበው ጥያቄ መሰረት ኮሚሽኑ የግብይት ዋጋው ውድቅ የተደረገበትን ምክንያት ጨምሮ ለጉምሩክ ዋጋ ውሳኔው መሰረት የሆነውን ምክንያት ለዲክላራሲዮን አቅራቢው በጽሁፍ መግለጽ አለበት፤ በጉዳዩ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ከመሰጠቱ በፊት ዲክላራሲዮን አቅራቢው ለተሰጠው ምክንያት ምላሽ እንዲሰጥ እድል ሊሰጠው ይገባል።

፲) የአዋጁ አንቀጽ ፻፩ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፻፩ ተተክቷል፤

፻፩. <u>የገንዘብ ምንዛሪ</u>

ወደ አገር ውስጥ የሚገቡም ሆነ ከአገር የሚወጡ ዕቃዎች የጉምሩክ ዋጋ የሚሰላው ስለዕቃዎቹ የቀረበው የዕቃ ዲክላራሲዮን ለኮሚሽኑ ቀርቦ ተቀባይነት ባገኘበት ቀን በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የተገለጸውን ጠቋሚ የገንዘብ ምንዛሪ ልክ በመጠቀም ይሆናል።

2/ Where the Commission, after receiving further information or evidence still has reasonable doubts about the accuracy of the declared value or in the absence of a response by the declarant, the customs value of the goods may be determined under the next applicable method provided in Articles 91 to 95 of this Proclamation.

3/ Upon written request, the Commission shall provide the declarant with the written reasons for the customs value determined, including the grounds for any decision rejecting the declared transaction value; The declarant shall be given an opportunity to respond to such reasons before a final determination is made.

10) Article 101 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new Article 101;

101. <u>Exchange Rate</u>

The customs value of imported or exported goods shall be calculated on the basis of the indicative exchange rate declared by the National Bank of Ethiopia on the date the customs declaration for the goods is submitted to and accepted by the Customs Commission.

፲፩) የአዋጁ አንቀጽ ፻፯ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፻፯ ተተክቷል፤

፻፯. <u>የዕቃዎች የሥሪት አገር መግለጫ</u>

፩/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ወደአገር በሚገቡ እያንዳንዱ ዕቃዎች እና/ወይም የእነዚህ ዕቃዎች ማሸጊያ የተሠሩበትን አገር የሚያስረዳ መግለጫ በቀላሉ ሊፋቅ፣ ሊነሳና ሊለወጥ በማይችል አኳኋን በእንግሊዝኛ ቋንቋ የተፃፈባቸው ሊሆን ይገባል።

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ ለንግድ የማይውሉ የግል መገልገያ ዕቃዎች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

፫/ ሚኒስቴሩ የሥሪት አገር መግለጫ የማይመለከታቸው ዕቃዎችን እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተዘረዘረውን ሳያሟሉ ወደ አገር የሚገቡ ዕቃዎች የሚስተናገዱበት ሁኔታን ጨምሮ የዕቃዎች ሥሪት አገርን የሚመለከት ዝርዝር መመሪያ ያወጣል።

፲፪) የአዋጁ አንቀጽ ፻፰ ተሰርዞ፣ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፻፰ ተተክቷል፤

፻፰. <u>በንግድ ስምምነት የታሪፍ ቅናሽ የሚደረግላቸው ዕቃዎች የሥሪት አገር ድንጋጌዎች</u>

፩/ የታሪፍ ቅናሽ የሚደረግላቸው ዕቃዎች የሥሪት አገር ድንጋጌዎች የሚመሩት ኢትዮጵያ አባል በሆነችባቸው ዓለም አቀፍ፣ አህጉራዊ፣ ቀጣናዊ ወይም በሁለትዮሽ የንግድ ስምምነቶች ውስጥ በተመለከቱ የስሪት አገር አወሳሰን ድንጋጌዎች መሰረት ብቻ ይሆናል።

11) Article 107 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new Article 107;

107. <u>Origin Marking</u>

1/ Without prejudice to the provision of Sub-Article (3) of this Article, the name of the country of origin of imported goods shall be affixed, in English, on each good and/or the package thereof in a manner that such marking cannot be easily deleted, removed or altered.

2/ The provision of Sub-Article (1) of this Article shall not apply to personal use items that are not intended for trade.

3/ The Ministry shall issue a detailed Directive concerning the country of origin, including goods that are not subject to origin marking, and the treatment of goods that do not fulfill the requirements set forth in Sub-Article (1) of this Article.

12) Article 108 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new Article 108:

108. <u>Rules of Origin under Preferential Trade Agreements</u>

1/ The preferential origin of goods shall be governed exclusively by the rules of origin laid down in the international, regional or bilateral agreements providing for preferential tariff treatments to which Ethiopia is a party.

፪/ የታሪፍ ቅናሽ ተፈጻሚ የሚሆነው አግባብ ባለው የታሪፍ ቅናሽ ስምምነት የተመለከተውን የሚያሟላ እና በስምምነቱ የተመለከተውን የስሪት አገርን የሚያሳይ ማስረጃ ሲቀርብ ይሆናል።

፫/ ኮሚሽኑ ኢትዮጵያ በምታደርጋቸው የታሪፍ ቅናሽ የንግድ ስምምነቶች እና በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት የሥሪት አገር ማስረጃዎችን የማስተዳደር፣ የማስፈጸም፣ የሥሪት አገር ማረጋገጫ የመስጠት እንዲሁም ትክክለኛነትን የማረጋገጥ ኃላፊነት ተሰጥቶታል፡፡

2/ The granting of preferential tariff treatment shall be conditional upon compliance with the applicable preferential rules of origin and the submission of valid proof of origin, as prescribed in the relevant agreement.

3/ The Commission shall be the competent authority responsible for the administration, implementation, issuance and verification of proofs of preferential origin, in accordance with the provisions of the relevant agreement and this Proclamation.

፲፫) የአዋጁ አንቀጽ ፻፲፰ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፩) ተተክቷል፤

፩/ በዚህ አዋጅ መሠረት የሚጠየቅ ዋስትና የጥሬ ገንዘብ ተቀማጭ፣ የባንክ የዋስትና ሰነድ፣ የኢንሹራንስ ቦንድ ወይም በመንግሥት በጀት የሚተዳደሩ መሥሪያ ቤቶችን፣ የመንግስት የልማት ድርጅቶችን እና ልዩ መብት የተፈቀደላቸው የኢኮኖሚ አንቀሳቃሾችን የሚመለከት ሲሆን በጽሑፍ የተደረገ የግዴታ ስምምነት ሊሆን ይችላል።

13) Sub-Article (1) of Article 118 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new Sub-Article (1):

1/ Where a security is required to be furnished pursuant to this Proclamation, such security shall be by cash deposit, bank guarantee, and insurance bond or in case of public bodies, public enterprises and authorized economic operators a written undertaking.

፲፬) የአዋጁ አንቀጽ ፩፻፳፫ ንዑስ አንቀጽ (፪) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፪) ተተክቷል፤

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት በብልጫ የተከፈለ ቀረጥና ታክስ ተመላሽ ጥያቄ ሊታይ የሚችለው ዕቃው የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ተከናውኖበት ዲክላራሲዮን ከተጠናቀቀበት ቀን ወይም ዕቃው ወደ አገር የማይገባ መሆኑ ተረጋግጦ ዲክላራሲዮኑ ከጉምሩክ መረጃ ሥርዓት ከተሰረዘበት ቀን ጀምሮ በሚቆጠር በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ከቀረበ ብቻ ነው፡፡

፲፭) የአዋጁ አንቀጽ ፩፻፴፫ ንዑስ አንቀጽ (፫) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፫) ተተክቷል፤

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) በተገለጸው መሠረት ለኮሚሽኑ ወይም ለህግ አስከባሪው አካል በተሰጠ መረጃ መሠረት የተገኙትን ዕቃዎች በቁጥጥር ስር እንዲውሉ ለማድረግ ከተቻለ መረጃና ድጋፍ ለሰጡ ሰዎች የገንዘብ ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ወሮታ ይከፈላል።

፬/ በባህሪው ሚስጥራዊ የሆነ ወይም ለጉምሩክ ዋጋ አወሳሰን ዓላማ በሚስጥር የተሰጠ ማንኛውም መረጃ እንደ ጥብቅ ሚስጥር መያዝ አለበት፤ መረጃውን የሰጠው ግለሰብ ወይም የመንግስት አካል ልዩ ፈቃድ ካልሰጠ በስተቀር፣ ይህ ሚስጥራዊ መረጃ መገለጽ የለበትም፤ ሆኖም መረጃው በፍርድ ቤት የክርክር ሂደት ውስጥ እንዲገለጽ ሲፈለግ ይህ ገደብ ተፈጻሚነት የለውም።

14) Sub-Article (2) of Article 123 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new Sub-Article (2);

2/ Any claim of refund of taxes and duties can be entertained on the basis of Sub-Article (1) of this Article only where the claim is lodged within one year from the date the customs formalities were completed and the declaration was finalized, or, in the event it is confirmed that the goods will not enter the country, from the date the declaration was deleted from the customs information system.

15) Sub-Article (3) of Article 133 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new Sub Article (3) ;

3/ Where the information supplied to the Authority or other law enforcement body pursuant to Sub-Article (1) of this Article leads to seizure of the goods, all persons that have provided information and support shall be rewarded in accordance with directive issued by the Ministry of Finance.

4/ All information which is by nature confidential or which is provided on a confidential basis for the purposes of customs valuation shall be treated as strictly confidential by the authorities concerned who shall not disclose it without the specific permission of the person or government providing such information, except to the extent that it may be required to be disclosed in the context of judicial proceedings.

፲፮) የአዋጁ አንቀጽ ፩፻፵፯ ንዑስ አንቀጽ (፫) ፊደል ተራ /ሀ/ እና /ለ/ ተሰርዘው በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፫) ፊደል ተራ /ሀ/ እና /ለ/ ተተክተዋል፡፡ እንዲሁም አዲስ ፊደል ተራ /ሐ/ ተጨምሯል፤

(ሀ) ዕቃዎቹን ለመደበቅ እንዲያስችል ሆኖ የተሠራ፣ የተለወጠ ወይም መደበቂያ አካል የተገጠመለት ከሆነ፤

(ለ) በፊደል ተራ (ሀ) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ማጓጓዣው የኮንትሮባንድ ዕቃ ጭኖ የተገኘ ከሆነ የተሽከርካሪው ባለቤት የገንዘብ ሚኒስቴር የሚያወጣው መመሪያ በሚወስነው መሰረት እንደነገሩ ክብደት እንዲሁም እንደጭነቱ መጠን በገንዘብ መቀጮ ወይም ማጓጓዣውን እስከመውረስ ሊያደርስ በሚችል ቅጣት ሊቀጣ ይችላል፤

(ሐ) ማጓጓዣው ከመወረሱ በፊት የማጓጓዣው ባለቤት ይህንኑ እንዲያውቀው ሊደረግ እና ማጓጓዣው ጥቅም ላይ ስለዋለበት ሁኔታ ማስረጃ እንዲያቀርብ እድል ሊሰጠው ይገባል።

፲፯) የአዋጁ አንቀጽ ፩፻፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፪) ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፪) ተተክቷል፤

፪/ ይግባኝ የተባለበት ጉዳይ የቀረጥና ታክስ ክፍያን የሚመለከት ሲሆን የፌዴራል ታክስ ይግባኝ ኮሚሽን ፶በመቶ (ሃምሳ በመቶ) ክርክር ያስነሳው የቀረጥና ታክስ ክፍያ መፈጸሙን ሳያረጋግጥ ይግባኙን አይቀበልም።

16) Paragraphs (a) and (b) of Sub-Article (3) of Article 147 of the Proclamation are deleted and replaced by the following new paragraphs (a), (b) and new paragraph (c) of Sub-Article (3) has been added;

(a) If it is constructed or modified or fitted with a compartment in a manner that enables it to conceal goods;

(b) Without prejudice to paragraph (a) of this provision, where a means of transport is found carrying contraband goods, the owner of the vehicle may, in accordance with a Directive to be issued by the Ministry of Finance, be subject to a monetary penalty determined based on the gravity of the offence and the quantity of the goods carried, or to a penalty that may extend to the confiscation of the means of transport;

(c) Prior to confiscation, the owner of the means of transport shall be notified and given the opportunity to present evidence or explanations regarding the use of the means of transport.

17) Sub-Article (2) of Article 155 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new Sub-Article (2) ;

2/ If the appeal is with respect to payment of duties and taxes, the Federal Tax Appeal Commission shall not admit lodging of the appeal unless 50% (Fifty percent) of the disputed duties and taxes have been paid.

፲፰) የአዋጁ አንቀጽ ፻፶፯ ንዑስ አንቀጽ (፫) ተሰርዟል፣ የአንቀጽ ፻፶፯ ቀሪ ድንጋጌዎች ተሸጋሽገዋል፡፡

፲፱) የአዋጁ አንቀጽ ፻፷ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፻፷ ተተክቷል፣

፻፷. <u>ስለ አጓጓዥ ግዴታዎች እና ኮንትሮባንድ በማጓጓዝ ድርጊት ስለ መሳተፍ</u>

፩/ ማንኛውም አጓጓዥ፡-

(ሀ) በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ የመንገደኞች ወይም የጭነት መግለጫ ካላቀረበ፤

(ለ) ከተፈቀደለት ሰው በስተቀር ሌላ ሰው ወደ ማጓጓዣው እንዲገባ ካደረገ ፤ወይም

(ሐ) ማጓጓዣው ከጉምሩክ ወደብ እንዲወጣ ከተወሰነ በኋላ ምክንያቱን ለጉምሩክ ሹም ሳያስረዳና ፈቃድ ሳያገኝ እንዲቆይ ካደረገ፤ ከብር ፬ሺ (አራት ሺ) ባላነሰ እና ከብር ፲ሺ (አስር ሺ) በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል፡፡

፪/ ማንኛውም አጓጓዥ የጉምሩክ ወደብ በደረሰ ማጓጓዣ ላይ የጉምሩክ ሹም በሌለበት ዕቃ የጫነ፣ ያራገፈ ወይም ለመጫን ወይም ለማራገፍ ሙከራ ያደረገ እንደሆነ ከብር ፲፭ ሺህ (አስራ አምስት ሺህ ብር) በማያንስና ከብር ፳ሺህ (ሀያ ሺህ ብር) በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል፡፡

18) Sub-Article (3) of Article 157 of the Proclamation is deleted and the remaining Sub-Articles of Article 157 are renumbered.

19) Article 160 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new Article 160 ;

160. <u>Obligations of Carriers and Participation in the Transportation of Contraband</u>

1/ **Any carrier who**:

(a) fails to submit a passenger manifest or cargo manifest within the prescribed time;

(b) permits any unauthorized person to enter the means of transport;or

(c) after the means of transport has been ordered to depart from the customs port, delays its departure without explaining the reason to, and obtaining permission from, the customs officer, shall be liable to a fine of not less than ETB 4,000 (Four Thousand Birr) and not more than ETB 10,000 (Ten Thousand Birr).

2/Any carrier who, after arrival at a customs port, loads, unloads, or attempts to load or unload goods without the presence or authorization of a customs officer shall be liable to a fine of not less than ETB 15,000 (Fifteen Thousand Birr) and not more than ETB 20,000 (Twenty Thousand Birr).

፫/ የኮንትሮባንድ እቃ ጭኖ የተገኘው ማጓጓዣ ባለቤት በኮንትሮባንድ ወንጀል ተሳታፊ ሆኖ ከተገኘ የሚኖርበት የወንጀል ተጠያቂነት እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ወንጀሉ እንዳይፈጸም ለማድረግ ተገቢውን የጥንቃቄ እርምጃ ካልወሰደ የኮንትሮባንድ እቃው መወረስ እንደተጠበቀ ሆኖ የተጫነውን የኮንትሮባድ ዕቃ ዋጋ አንድ መቶ ፐርሰንት ወይም ብር ፪፻ሺህ (ሁለት መቶ ሺህ ብር) ከሁለቱ አነስተኛውን የገንዘብ መቀጫ ይቀጣል፡፡

፬/ የማጓጓዣው ባለቤት ሰነዶችን የማጣራት፣ የፍተሻ፣ እና የማሸግ እርምጃዎችን ጨምሮ በጉምሩክ ደንብ የተመለከቱ የጥንቃቄ እርምጃዎችን በመውሰድ ረገድ የተከተለውን አሰራር ከግምት ውስጥ በማስገባት የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) ድንጋጌ የስራውን ልዩ ባህሪ መሰረት በማድረግ ለህዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪም ተፈጻሚ ይሆናል።

፭/ የጭነት ማሸጊያን ወይም ኮንቴነርን በመክፈት የኮንትሮባንድ ዕቃን ቀላቅሎ ጭኖ የተገኘ ማጓጓዣ ባለቤት ዕቃው መወረሱ እንደተጠበቀ ሆኖ የማጓጓዣው ባለቤት ብር ፭፻ሺህ ብር (አምስት መቶ ሺህ ብር) የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

3/ Without prejudice to any criminal liability where the owner of a means of transport is found to have participated in a contraband offence, if he owner has not taken preventive measures to prevent the crime shall be liable to administrative penalty of one hundred percent of the value of the contraband goods loaded or Birr 200,000(Two Hundred Thousand Birr) whichever is lesser, In addition to confiscation of the means of transport.

4/ The provisions of Sub-Article (3) of this Article shall also apply to a public transport vehicles, consideri ng the specific operational circumstances and to the extent to which the owner has complied with preventive obligations explicitly set out in the customs regulations, including documentation,inspection and sealing requirements.

5/ The owner of a means of transport found to have loaded contraband goods by mixing them after opening a cargo seal or container shall, without prejudice to the confiscation of goods, be punished with a fine of Birr 500,000 (Five Hundred Thousand Birr).

፮/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) የተመለከተው ማጓጓዣ እንስሳ ከሆነ ባለቤቱ የተጫነውን የኮንትሮባንድ ዕቃ አንድ መቶ ፐርሰንት ወይም የእንስሳው ወቅታዊ ዋጋ የገንዘብ መቀጫ ከሁለቱ አነስተኛውን የገንዘብ መቀጫ ይቀጣል፡፡

፯/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) እና (፬) የተመለከተው ቢኖርም በማንኛውም ሁኔታ በማጓጓዣው ባለቤት ላይ የሚጣለው መቀጫ ከማጓጓዣው ወቅታዊ የገበያ ዋጋ መብለጥ የለበትም፡፡

፳) የአዋጁ አንቀጽ ፩፻፷፩ ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ ፩፻፷፩ ተተክቷል፡፡

፩፻፷፩. <u>የጉምሩክ መጋዘን ፈቃድ ግዴታዎችን ያለማክበር</u>

፩/ ማንኛውም የጉምሩክ መጋዘን ባለፍቃድ በዚህ አዋጅ የተመለከቱትን ግዴታዎች ያላከበረ እንደሆነ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፩፻፸፮ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሰረት በሚወጣ መመሪያ ላይ ተመስርቶ ሊወሰድ የሚችል ተጨማሪ አስተዳደራዊ እርምጃ እንደተጠበቀ ሆኖ ከብር ፩፻ ሺህ (አንድ መቶ ሺህ) በማያንስና ከብር ፪፻ ሺህ (ሁለት መቶ ሺህ) በማይበልጥ መቀጫ ይቀጣል፡፡

6/ If the means of transport referred to under Sub-Article (3) of this Article is an animal, the owner shall be liable to a monetary penalty equal to one hundred percent (100%) of the value of the contraband goods loaded on the animal or the current market value of the animal, whichever is lesser.

7/ Notwithstanding the provisions of Sub-Articles (3) and (4) of this Article, in any case, the penalty imposed on the owner of the means of transport shall not exceed the current market value of the means of transport.

20) Article 161 of the Proclamation is deleted and replaced by the following new Article 161:

161. <u>Failing to Adhere to the Obligations of Customs Warehouse Licensee</u>

1/ Any licensed customs operator who fails to comply with the obligations specified in this Proclamation shall, without prejudice to additional administrative measures that may be taken based on the Directive to be issued pursuant to Article 176 Sub-Article (3) of this Proclamation, pay a fine of not less than Birr 100,000 (One Hundred Thousand Birr) and not exceeding Birr 200,000 (Two Hundred Thousand).

፪/ ወደ ጉምሩክ ቦንድድ መጋዘን መግባት ያለበት ዕቃ ወደ ጊዜያዊ ዕቃ ማከማቻ መጋዘን ገብቶ የተገኘ በሚሆንበት ጊዜ በአምስት የስራ ቀናት ውስጥ ወደ ተፈቀደ የጉምሩክ መጋዘን ያልተላለፈ ዕቃ አስመጪ ብር ፲ ሺህ (አስር ሺህ ብር) መቀጫ ከፍሎ ዕቃውን ወደ ቦንድድ መጋዘን እንዲያስተላልፍ ወይም ዕቃው በጊዜያዊ የዕቃ ማከማቻ መጋዘን ውስጥ እያለ የጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት እንዲፈጸምበት ያደርጋል፡፡

፫/ ወደ ሀገር ውስጥ በጊዜያዊነት የገባ ዕቃ በአዋጁ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ተመልሶ ከአገር ያልወጣ እንደሆነ አስመጪው በእርጅና ቅናሹ ላይ የሚከፍለው ቀረጥና ታክስ እንዲሁም ሌሎች ወጪዎችን መክፈሉ እንደተጠበቀ ሆኖ ብር ፪ መቶ ሺህ (ሁለት መቶ ሺህ) መቀጫ ከፍሎ የተያዘው ዋስትና ተመላሽ ተደርጎለት በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ዕቃው ተመልሶ ከአገር እንዲወጣ ያደርጋል፡፡

፳፩) የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

ይህ አዋጅ ከጸናበት ቀን በፊት ተጀምረው ፍጻሜ ያላገኙ ጉዳዮች በነባሩ አዋጅ መሰረት ፍጻሜ ያገኛሉ፡፡

2/ where the goods that should have entered a customs bonded warehouse are found to have entered a temporary storage warehouse, and the goods are not transferred to the authorized customs warehouse within five working days the importer shall pay a fine of Birr 10,000 (Ten Thousand Birr) and transfer the goods to a bonded warehouse or ensure that customs formalities are completed while the goods are in the temporary storage warehouse.

3/ Where goods imported into the country on a temporary basis are not reexported within the period specified in the Proclamation, the importer shall, without prejudice to the payment of duties and taxes based on the depreciated value as well as other expenses, pay a fine of Birr 200,000 (Two Hundred Thousand Birr) have the held security returned and ensure the goods are reexported within one month.

21) Transitory Provision

Pending cases started before the issuance of this Proclamation shall be settled based on the provisions of the amended Proclamation.

፫. <u>አዋጁ የሚጸናበት ቀን</u>

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ ሐምሌ ፲፮ ቀን ፪ሺ፲፰ ዓ.ም

ታዬ አፅቀስላሴ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

3. <u>Effective Date</u>

This Proclamation shall enter into force on the date of its publication in the Federal Negarit Gazette.

Done at Addis Ababa, On this 23rd day of July 2026

TAYE ATSKESELASSIE

PRESIDENT OF THE FEDRAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA